በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁጥር OFAG/F.02/1/16
ቀን 25/07/2012

ለክቡር ዶ/ር ኢንጅነር ስለሺ በቀለ

የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር እና

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቦርድ ሰብሳቢ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል፣</u>

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰውን ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 9 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 12 ገጽ የሂሣብ መግለጫዎች ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከማክበር ከሰላምታ ጋር

ወርቅአፈራሁ ወንድሙ
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ (ከ9 ገጽ የኦዲት ሪፖርት፣ 36 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች እና 23 ገጽ አባሪ ጋር)
  <u>ባህር ዳር፣</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ
የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ዩኒቨርሲቲው የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣

ዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፦

1. በማዕከል ፋይናንስ ከሚገኙ የፕሮጀክት ሂሳቦች ውስጥ 9 ፕሮጀክቶች በአጠቃላይ ድምር ብር 453,103.29 ከወጪ ቀሪ ያላቸው ሲሆን ፕሮጀክቶቹ የተቋረጡ ሲሆን ገንዘቡ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
2. በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጁ ህንድ አገር ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ ተማሪዎች ብር 4,066,673.32 እና በባህርዳር ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ሱዳን አገር ለሚማሩ ተማሪዎች ብር 739,809.00 በድምሩ ብር 4,806,482.32 የተከፈለ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው በበጀት ዓመቱ ለውጭ አገር ስልጠና በ6272 የሂሳብ መደብ በጀት ያልያዘና ክፍያው በ6271 በሀገር ውስጥ ስልጠና የሂሳብ መደብ የተመዘገበ

መሆኑ፤እንዲሁም የተከፈለው ክፍያ ዩኒቨርስቲው ተማሪዎቹ ከሚማሩበት ተቋም ጋር ውል በመግባት ክፍያውን መፈጸም ሲገባው ገንዘቡን ለትምህርት በሄዱት መምህራን የባንክ ሂሳብ ገቢ በማድረግ የክፍያውን ማስረጃ መምህራኑ አቅርበው እንዲያወራርዱ የተደረገ መሆኑ፤

3. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀፅ 100 ንዑስ አንቀፅ 3 ለትርፍ የቆመ ድርጅት ካልሆነ በስተቀር ክልሎች በፌዴራሉ መንግስት ንብረት ላይ የፌዴራሉ መንግስትም በክልሎች ንብረት ላይ ግብር ወይም ቀረጥ የማስከፈል ስልጣን እንደማይኖራቸዉ የተደነገገ ሲሆን ዩኒቨርስቲው ለባህርዳር ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት የ2009 ውዝፍ ዓመታዊ የቦታ ግብር ብር 2,811,268.40 እና እንዲሁም የ2010 ዓመታዊ የቦታ ግብር ብር 2,811,268.40 በድምሩ ብር 5,622,536.80 ከመመሪያ ውጭ የከፈለ መሆኑ፤

4. ዩኒቨርሲቲው በ2008 በጀት ዓመት የጽዳት እቃዎች ግዥ ለመፈጸም ባወጣው ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ አስመጪው 75,163 መወልወያዎች በብር 1,305,581.31 ለማቅረብ ከዩኒቨርሲቲው ጋር ውል የገባ ሲሆን ለአቅራቢው በድምሩ የ15,650 መወልወያ ብር 271,840.50 ንብረቱ ገቢ ተደርጓል በሚል የተከፈለ ሲሆን ቀሪው 59,513 መወልወያ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ሳይደረግና የዕቃ ገቢ ደረሰኝም ሆነ ጊዚያዊ መረካከቢያ ቅጽ ሳይኖር ዩኒቨርሲቲው በጥራት ኮሜቴ አንዴ ትክክል መሆኑ የተረጋገጠን ንብረት አልረከብም ብሏል በማለት በፍርድ ቤት ውሳኔ የውሉ ቀሪ ገንዘብ ብር 1,032,505.55 ፤ ወለድ ብር 191,797.15 እና የጠበቃ አበል ብር 103,250.55 በድምሩ ብር 1,327,553.25 በቀን 30/8/2011 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 599106 ዩኒቨርሲቲው ገቢ ላላደረገው (ላልተረከበው) መወልወያ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተከፈለ መሆኑ፤

5. ዩኒቨርሲቲው ዘላቂነት ባላቸው የስራ መደቦች ላይ ቋሚ ሰራተኞች ቀጥሮ ማሰራት ሲገባው የቀን ሰራተኞችን በውል ስምምነት በማሰራት **በድምሩ ብር 2,966,594.51** ለቀን ሰራተኞች ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

6. የግዢ ፍላጎትን ከየክፍሉ በማሰባሰብ ግልፅ ጨረታ በማውጣት የተለያዩ ድርጅቶችን በማሳተፍ ግዢ መፈጸም ሲገባ በዋናው ግቢ (ማዕከላዊ ፋይናንስ) የተለያዩ

ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎችና ሼልፎች ግዢ በድምሩ በብር 479,261.95፣ በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የተለያዩ ዕቃዎች ግዢ በብር 2,505,279.32፣ እንዲሁም በሳይንስ ኮሌጅ ማሪታየም አካዳሚ የተለያዩ ኬሚካሎችና እቃዎች ግዢ በብር 2,125,103.39 በድምሩ በብር 5,109,645.26 የተለያዩ ዕቃዎች ግዢ በዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) ግዢ የተፈጸመ መሆኑ፣

7. **በሂውማኒቲ ኮሌጅ** ብር 110,000.00 እና **በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ** ብር 363,819.78 በድምሩ ብር 473,819.78 የወጪ ሂሣብ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ መሆኑ፤

8. ከመደበኛና ካፒታል በጀት ብር 4,991,384.60 እና ከውስጥ ገቢ ብር 4,739,984.44 በድምሩ ብር 9,731,369.04 በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤

9. ከመደበኛና ካፒታል በጀት ብር 1,717,972.98 እና ከውስጥ ገቢ ብር 65,728.47 በድምሩ ብር 1,783,701.45 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤

ከላይ በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሣ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

1. <u>ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)</u>

1.1 **የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** በቀን 29/6/2011 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 25674 በሂሳብ መደብ 6313 ለእንቦጭ አረም ማስወገጃ ማሽን ግዢ ብር 19,272,510.00 ለሙላት ኢንዱስትሪያል ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የከፈለ ሲሆን ፦

- ✓ ማሽኑ እንዲገዛ/እንዲሰራ በየትኛው አካል ጥያቄ እንደቀረበ የሚያሳይ ሰነድ የሌለ መሆኑ፤

- ✓ ማሽኑ ማክሰኝት ወረዳ የሻ ማንጌ ቀበሌ አባቴ ጎጥ የጣና ሐይቅ አካባቢ ከደረሰበት ጊዜ አንስቶ አንድ ጊዜ ብቻ እንደሰራና አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፤
- ✓ በባለቤትነት የሚረከበው አካል ባለመኖሩና ስራውን እየሰራ ካለመሆኑም በተጨማሪ ማሽኑ መቀመጥ/ማረፍ ያለበት በሃይቁ ላይ መሆን ሲገባው ለብልሽትና ለተጨማሪ ወጪ በሚዳርግ ሁኔታ በምድር ላይ የሚገኝ መሆኑ፤
- ✓ በሃይቁ ጫፍ ላይ ተሰርቶ የነበረው ኮንቬር የሚባል ማሽን ውሃው ሲጎል እንደሚችል ታስቦ መሰራት ሲገባው ባለመሰራቱ በአሁኑ ሰዓት ኮንቬሩ መሬት ላይ ሲሆን ማሽኑን ስራ ለማስጀመር ወደ ውሃው እንዲገባ ተደርጎ እንደገና ካልተሰራ አስቸጋሪ መሆኑ፤

በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ የገዛው የእንቦጭ አረም ማስወገጃ ማሽን ከአንድ ዓመት በላይ ያለአገልግሎት ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ተቀምጦ የሚገኝ ሲሆን ማሽኑ በዚሁ ከቀጠለ ለብልሽት የሚዳረግ መሆኑ፤

1.2 **በግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ** በአደጋ መከላከል የትምህርት ክፍል የባንክ ሂሳብ ቁጥር (B=1000224654913) ብር 25,014.76 እና በስነ ምድር የትምህርት ክፍል የባንክ ሂሳብ ቁጥር (B=1000224656867) ብር 239,187.04 በድምሩ ብር 264,201.80 በሰኔ 30/2011 የተመለከተ የባንክ ከወጪ ቀሪ (balance) ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ መደረግ ሲገባው ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፤

1.3 በዩኒቨርሲቲው በመከናወን ላይ የሚገኙ የግንባታ ሥራዎች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ መከናወናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ✓ በሳምሶን ገ/ዮሐንስ ህንፃ ስራ ተቋራጭ በቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ኮሌጅ የሚገነባው የመማሪያ ክፍሎች እና ክሊኒክ በውሉ መሠረት በ03/13/2007 መጠናቀቅ የነበረበት ቢሆንም የውል ማራዘሚያ 489 ቀናት ተጨምሮ እስከ ሰኔ 30/2011 ሥራው ያልተጠናቀቀና ያለበት የስራ ደረጃ 76% መሆኑ፤
- ✓ በእቴቴ ኮንስትራክሽን በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የሚገነባው ግንባታ BIT Class Room and Laboratory Lot-2 በውሉ መሠረት በ28/05/2010 መጠናቀቅ

የነበረበት ቢሆንም የውል ማራዘሚያ 386 ቀናት ተጨምሮ እስከ ሰኔ 30/2011 ሥራው ያልተጠናቀቀና ያለበት የስራ ደረጃ 87% መሆኑ፤

✓ በአውስኮድ በደብረ ማርቆስ ከተማ ለሚገነባው የርቀት ትምህርት ማስተባበሪያ በውሉ መሠረት በ16/10/2010 መጠናቀቅ የነበረበት ቢሆንም የውል ማራዘሚያ 337 ቀናት ተጨምሮ እስከ ሰኔ 30/2011 ሥራው ያልተጠናቀቀና ያለበት የስራ ደረጃ 72% መሆኑ፤

1.4 ለዩኒቨርሲቲው በ2011 በጀት ዓመት በተለየየ የሂሳብ አርእስት የተደለደለው በጀት እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲነጻጸር በተለያዩ ሂሣብ መደቦች ከመደበኛ በጀት ብር 157,444,177.31 እና ከውስጥ ገቢ ብር 23,759,376.74 በድምሩ ብር 181,203,554.05 ሥራ ላይ ያልዋለ (ያልተሰራበት) መሆኑ፤

2 ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)

2.1 የዩኒቨርሲቲው የንብረት አመዘጋገብ፤ አያያዝ እና አጠባበቅ በፌደራል መንግስት ግገርና ንብረት አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 649/2001 መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

1. **በኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፤**

   በፕሮጀክት ዕቃ ግምጃ ቤት፣

   - ስቶሮች በሙሉ በቆርቆሮ የተሰሩ መሆኑ፤
   - የማይሰራ ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ ስካነር ብዛት 2፣ ፕሪንተር፣ ኮምፒውተር Dell ብዛት 4፣ ኮምፒዩተር ብዛት 6፤ ላፕቶፕ ብዛት 28፤ UPS፤ ስታብላይዘር ብዛት 19 ያለአገልግሎት በዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኙ መሆኑ፤

   በቋሚና አላቂ ግምጃ ቤት፤

   - በ2010 የተገዛ ተሽከርካሪ ወንበር ያለአገልግሎት በግምጃ ቤት የሚገኝ መሆኑ፤

2. **በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ**

   በአላቂ፤ ቋሚና ባዮ ሜዲካል ግምጃ ቤት፤

   - በ2009 እና በ2010 የገቡ ያለአገልግሎት የተቀመጡ የሰራተኛ የደንብ ልብስ (የተለያዩ መጠን ያላቸው ሸሚዝ ብዛት 373፣ የሴት ጫማ ብዛት 116፣ የወንዶች ጫማ ብዛት 105) የሚገኙ መሆኑ፤

- ያገለገሉ የአውቶስስ መኪና ባትሪ ብዛት አንድ፣ ያገለገሉ የመኪና ጎማዎች ብዛት 22፣ ያገለገለ ፕሮጀክተር ኤልሲዲ፣ ያገለገለ ተሽከርካሪ ወንበር፣ ያገለገለ ሞተር ሳይክል (ሱዚኪ) 4- ደማ 2050 ብዛት 1 በግምጃ ቤቱ የሚገኙ መሆኑ፤

በመድሃኒት ስቶር፤

- የመድሀኒቶች ገቢና ወጪ በሞዴል 19 እና 22 በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፤
- በግምጃ ቤቱ በቂ ፍሪጅ የሌለ መሆኑ፤

3. **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት**

በአላቂ እቃ ግምጃ ቤት፤

- በ2009 ዓ.ም የተገዛ ያለአገልግሎት የተቀመጠ በቁጥር 352 ሽሚዝ ሚገኝ መሆኑ፤
- የተለያየ ቁጥር የወንድ እና የሴት ጫማ ብዛት ከ461 በላይ የሚገኝ መሆኑ፤

በተመላሽ እቃ ግምጃ ቤት፤

- የተበላሹ ዲስክ ቶፕ ኮምፒዩተር ብዛት 26፣ ላፕቶፕ ብዛት 68፣ ፕሪተር 22፣ ፎቶ ኮፒ ብዛት 2፣ የላብራቶሪ ማሽን ብዛት 1፣ የውኃ ማጣሪያ ማሽን ብዛት 3፣ ዩፒኤስ 100 ዋት ብዛት 56፣ ቴሌቭዥን 5፣ ፋክስ ብዛት 1፣ ስካነር ብዛት 1፣ ጎማ ብዛት 4፣ ጀነሬተር ብዛት 1፣ ካዝና ብዛት 3 በግምጃ ቤት የሚገኙ መሆኑ፤

4. **በማዕከላዊ ግቢ (ዊዝደም ግቢ) የዕቃ ግምጃ ቤት፤**

- ለግምጃ ቤቱ መስኮቶች ፍርግርግ ብረት (ግሪል) ያልተሰራ እና ግምጃ ቤቱ ከጉኑ ካሉ ቢሮዎች (መዝገብ ቤት እና የንብረት አስተዳደር ጸሃፊዎችና ባለሙያዎች ክፍል) የተለየው በመስታወት መለያ (ፓርቲሽን) እና በሸቦ መሆኑ፤
- የማይሰራ ኮምፒውተር ብዛት 2 (ሁለት) እና ረጅም ጊዜ የቆዩ የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ (ዲቫይደር) የሚገኙ መሆኑ፤
- በ2009 ገቢ የተደረገ ብዛት 6,878.00 ሽሚዞች፤ የወንድ ካራባት ብዛት 3875፤ የሴቶች ካራባት ብዛት 2,999 እና 6 አዳዲስ ትልቅ የእጅ ጃንጥላዎች ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2.2 የዩኒቨርስቲው ተሽከርካሪዎች በፌደራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሠረት መያዛቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የ15 ተሽከርካሪዎች የኪሎ ሜትር ቆጠሪ (ጌጅ) የማይሰራ መሆኑ፤ 2 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸው መሆኑ እና 2 ተሽከርካሪዎች (ትራክተሮች) የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል።

2.3በዩኒቨርሲቲው የሰው ኃይል መዋቅር መሠረት ዳይሬክተሩን ጨምሮ 23 የኦዲት ባለሙያ የሚያስፈልግ ቢሆንም አሁን ያለው የሰው ሃይል ግን 13 ብቻ መሆኑ እና ቀሪው 10 የፋይናንሻልና የንብረት ከፍተኛ ኦዲተር የስራ መደብ ያልተሟላ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

2.4የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የዩኒቨርሲቲውን የ2009 እና 2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ዩኒቨርሲቲው ተገቢውን እርምጃ የወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

<u>የ2010 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝት፤</u>

- በዩኒቨርሲቲው በተለያዩ የንግድ ሥራ ዘርፎች የተሰማሩ 27 ድርጅቶች የሚገኙ ሲሆን ለተቋሙ ምንም ዓይነት ገቢ የማያደርጉ መሆኑ፤
- ተቋሙን ለቀው ለሄዱ ሠራተኞች አላግባብ ከተከፈለው የደመወዝ ሂሳብ ብር 5,022.20 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- በግሽ አባይ ግቢ የ2008 በጀት ዓመት የ268 ሰራተኞች የዓመት እረፍት ፈቃድ ወደ ገንዘብ ተለውጦ በወጪ ማመስከሪያ ቁጥር 51412 ሊከፈላቸው ከሚገባው የገንዘብ መጠን በላይ በድምሩ ብር 189,968.54 በብልጫ የተከፈለ እና በህክምናና ጤና ሣይንስ ኮሌጅ ብር 6,6324 ሊከፈላቸው ከሚገባው የገንዘብ መጠን በላይ ብር 9,348.46 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤ በጠቅላላው ድምር ብር 199,317.00 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤
- ለባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ለዓመታዊ የቦታ ግብር በቀን 19/08/2010 በባንክ ወጪ ማስከመሪያ ቁጥር 594360 ብር 2,833,663.40 አላግባብ የተከፈለ መሆኑ፤
- በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ኮሌጆች በድምሩ በብር 11,032,804.02 ያለውደድር በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፤
- የግንባታ ሥራ ከቋረጡ ሥራ ተቋራጮች የሚፈለግ የቅድሚያ ክፍያ በድምሩ ብር 10,967,474.86 (750,995.56 + 10,216,479.30) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

የ2009 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝት፤

- በ2008 በጀት ዓመት በዩኒቨርሲቲው ድጋፍ ትምህርታቸውን ተምረው የውል ግዴታቸውን ካልተወጡ መምህራን መሰብሰብ የነበረበት ብር 2,839,320.13 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

በ2007 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝት፤

- ዩኒቨርሲቲው በግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ ለተማሪዎች ማደሪያ የሚያገለግል ህንጻዎች ግንባታ ከA.M.B ኮንስትራክሽን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጋር የሎት 2 ግንባታ በብር 62,114,548.65 በ730 ቀናት እንዲጠናቀቅ እና የሎት 4 ግንባታ በብር 40,796,914.49 በ540 ቀናት እንዲጠናቀቅ ውል የተገባ ቢሆንም ግንባታው በመዘግየቱ ምክንያት ሎት ሁለት 49.63% እና ሎት አራት 85.53% ላይ እንደደረሰ የግንባታ ውሉ እንዲቋረጥ የተደረገ ሲሆን እስከ 2007 በጀት አመት ማጠናቀቂያ ድረስ ርክክብ ባለመደረጉ በዩኒቨርሲቲው የመማር ማስተማርም ሆነ ሃብት ብክነት ላይ ላደረሰው ጉዳት የጉዳት ካሳ እንዲከፍል (እንዲቀጣ) ያልተደረገ መሆኑ፤

ከላይ የተዘረዘሩት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያሳሰብን ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም።

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት